# የግብር ምላሽዎ በዚህ አመት ሊዘገይ ይችላል።

## *ለተገኘ ገቢ ግብር ክሬዲት (ኢአይቲሲ) (Earned Income Tax Credit (EITC) እና የተጨማሪ ልጅ ግብር ክሬዲት (ኤሲቲሲ) (Additional Child Tax Credit (ACTC)) ተቀባዮች አስፈላጊ መረጃ*



የተገኘ ገቢ ግብር ክሬዲት (EITC) ወይም ተጨማሪ የህጻን ግብር ክሬዲት (ACTC) የሚቀበሉ ከሆነ አዲሱ ፌዴራል ህግ የግብር ምላሽዎን እስከ ፌብሩዋሪ 15, 2017 ድረስ ያዘገየዋል።



### *ማወቅ የሚገባዎት*

- ✔ **ግብርዎን ሁልጊዜም እንደሚያደርጉት ይሙሉ።** ግብርዎን የሚያሰሩበትን ጨምሮ፣ የግብር ምላሽዎን የሚያሰሩበትን መንገድ መቀየር የለብዎትም። መዘገየቱ የሚያጋጥመው ለሁሉም የግብር መሙያ መንገዶች ነው (ቪታ ቦታዎች (VITA sites)፣ በንግድ የግብር አዘጋጅ እና በራስ ማዘጋጀት)። እነዚህን የግብር ክሬዲቶችን ለሚጠይቁ፣ ተመላሾች ከፌብሩዋሪ 15 በፊት አይሰጡም። ከዚህ የተለየ ምንም አይኖርም።

- ✔ **በዘገዩ ምላሾች ላይ የተመሰረቱ የብድር አቅርቦቶችን፣ እንደ በደብሊው-2 (W-2) ላይ ሳይሆን በአመቱ መጨረሻ የክፍያ ስታብ ላይ የተመሰረቱ የምላሽ ጥያቄዎችን የመሳሰሉትን፣ ይጠንቀቁ።** የብድር ክፍያዎች ውድ ናቸው፤ እንዲሁም ያለ ሁሉም የገቢ መረጃ ምላሹ ትክክለኛ ላይሆን ይችላል። እነዚህ ችግሮች ቢኖሩም እንኳን፣ ኦሪጅናሉ ብድር መከፈል ይኖርበታል።

- ✔ **ምንም እንኳን አይአርኤስ (IRS)፣ ኢአይቲሲ (EITC) እና ኤሲቲሲ (ACTC) ምላሾችን በፌብሩዋሪ 15 ጀምሮ መስጠት ቢጀምርም፣ የሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች ተመላሻቸውን እስከ ፌብሩዋሪ 27 ሳምንት ድረስ በማከናወኛ ጊዜያት የተነሳ ላያገኙ ይችላሉ።**

- ✔ **ኢአይቲሲ (EITC) እና ኤሲቲሲ (ACTC) ምላሾችን የማይጠይቁ ግብር ከፋዮች ሆነ ከፌብሩዋሪ 15 በሁዋላ የሞሉ ኢአይቲሲ (EITC) እና ኤሲቲሲ (ACTC) ምላሾችን የሚጠይቁ ግብር ከፋዮች በዚህ ምንም አይነኩም።**

- ✔ **አንዴ ከሞሉ፣ የፌዴራል ግብር ምላሽ ሁኔታዎን** በአይአርኤስ (IRS) ተመላሼ የት አለ በሚለው መገልገያ በ www.irs.gov/refunds ማወቅ ይችላሉ።

## ብቁ ነዎትን?

### ኢአይቲሲ (EITC)

ኢአይቲሲ ለሰራተኛ ህዝብ የሚሰጥ የግብር ክሬዲት ነው። ብቁ ለመሆን፣ በ2016 ያገኙት ጠቅላላ ገቢ ከነዚህ መብለጥ የለበትም፥

- $47,955 ($53,505 አግብተው አንድ ላይ የሚሞሉ) ከሶስት ወይም ከዛ በላይ የሚያሙዋሉ ህጻናት ጋር
- $44,648 ($50,198 አግብተው አንድ ላይ የሚሞሉ) ከሁለት የሚያሙዋሉ ህጻናት ጋር
- $39,296 ($44,846 አግብተው አንድ ላይ የሚሞሉ) ከአንድየሚያሙዋሉ ህጻን ጋር
- $14,880 ($20,430 አግብተው አንድ ላይ የሚሞሉ) ግን ህጻን የሌላቸው

### ኤሲቲሲ (ACTC)

ኤሲቲሲ ተመላሽ የሆነ የግብር ክሬዲት ሲሆን የሚሰጠውም ከሙሉ በታች የህጻን የግብር ክሬዲት ለሚያገኙት ነው። ምንም እንኳን ምንም ግብር ባይጣልብዎትም፣ የተጨማሪው የህጻን ግብር ክሬዲት ተመላሽ ሊሰጥዎ ይችላል።

*ለነዚህ ግብር ክሬዲቶች ስላለዎት ብቁነት ተጨማሪ ለማወቅ፣ እባከዎትን ነጻ የቪታ ቦታ በ montgomerycountymd.gov/freetaxhelp ወይም የግብር አዘጋጅዎን ያናግሩ።*

### ተጨማሪ መረጃዎች

ስለነዚህ የግብር ክሬዲቶች ተጨማሪ መረጃ እና በ ቪታ ቦታ (VITA sites) የሚገኘውን ወይም ለነጻ ኦንላይን ማመልከቻ ነጻ የግብር ማዘጋጃ አገልግሎቶችን ለመረዳት፣ እባከዎትን ይህንን ድረገጽ ይጎብኙ montgomerycountymd.gov/cashback አይአርኤስ ያሰለጠናቸው የግብር አዘጋጆች ጥያቄዎችዎን ሊመልሱ እና በነጻ እንዲሞሉ ሊያግዙዎትን ይችላሉ። ስለጠቅላላ የግብር ክሬዲቶች ተጨማሪ መረጃ በ IRS.gov ላይ ይገኛል።

*የማህበረሰብ ድርጊት ወኪሉ ነጻ የበጎ ፈቃድ የገቢ ግብር ርዳታ (VITA) ትብብር ከአይአርኤስ የተረጋገጡ የግብር ፕሮፌሽናሎች እና በጎ አድራጊዎች ጋር በመሆን የዝቅተኛ እና መሃከለኛ ገቢ ቤተሰቦች የግብር ምላሻቸውን እና ክሬዲታቸውን ለማስጨመር፣ ኢአይቲሲ (አርንድ ገቢ ግብር ክሬዲት)ን ጨምሮ፣ ይሰራል። ቤተሰብዎ በአመት ከ $54,000 በታች ካገኙ፣ ነጻ የግብር ርዳታ እና የ 2016 ፌዴራል እና ስቴት ምላሽዎን በ "ኢፋይሊንግ (e-filling)" አማካይነት በፍጥነት ማግኘት ይችላሉ። "ነጻ" የቁጠባ ሂሳብ መክፈት እና በዩኤስ ቁጠባ ቦንድ መቆጠብ ይችላሉ። የተረጋገጠ ተቀባይ ወኪል አይቲአይኤንዎችን እንዲያገኙ ሊያግዝዎት ይችላል።*